18/09/2011

# የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ዘመቻ ደመላሽ ህዝባዊ የድጋፍ ጥሪ!

የተከበራችሁ በመላው አለም የምትገኙ ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን በሙሉ

እኛ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ሰራዊት አባላት በሃገራችን የተንሰራፋውን ጸረ ህዝብና ዘረኛ ስርዓት በመፋለም ለአመታት ትዳር ልጅ  ቤት ንብረት ሳንል በየበረሃው በየዱር  ገደሉና ሸንተረሩ መስዋዕትነትን በመክፈል ላይ መሆናችን ለናንተ የተሰወረ አይደለም።

በሰፊው በተንቀሳቀስንባቸው የሃገሪቱ ሰሜናዊ ክፍሎች የህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይን የግድያ ሰራዊት አደባይተነዋል፡ልዩ የስለላና የግድያ ታጣቂዎችንም ዳግም እንዳይመለሱ በማድረግ ቀጥተናቸዋል። ዘረኛው ስራት የሃገሪቱን አንጡራ ሃብት ወደውጭ የሚያግዋጉዝበትን የኢትዮ ሱዳን መንገድ በማጠር ዝርፊያውን ገተነዋል አሊያም በብርጌድ ጦር ታጅቦ እንዲሄድ አስገድደነዋል።

እኛ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ተዋጊዎች አላማችን አንድና አንድ ነው። ዛሬ በህዝባችን ትከሻ ላይ በተለያየ ዘደ ተቀምጦ በማን አለብኝነት ለሃያ አመታት የሚገድለውን የሚያስረውን የሚያሰቃየውንና የሚያሳድደውን ዘረኛ የገዳዮች ስብስብ በሃይል ለመጣልና በሃገራችን ላይ ህዝባዊና ደሞክራሲያዊ ስራት እስከሚቆም ድረስ የህዝብ ዘበኛ ሆኖ ማገልገል ነው።

የሃገር ዳር ድንበር ሲገሰስ፡የህዝብ ባህልና ስራት ሲፈርስ ፡ የዜጎች ደም ሲፈስ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ ይቆማል ይፋለማል። ገዳዮቹንና በላኤ ሰቦችንም ይበቀላል በህይወት እስካሉም ድረስ እያሳደደ ለፍርድ ያቀርባል።

የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ተዋጊዎች በወልቃይት ጸገዴና ጠለምት፣, በአርባ ጉጉና በበደኖ፡ እንዲሁም በጋምቤላ ህዝቦቻችን ላይ የደረሰው ጅምላ ፍጅት እንዲሁም የዘር ማጥፋት ግፍ እንደ እግር እሳት ያቃጥለናል፤ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ኢሰባዊ ግድያ ያንገበግበናል፤ ከምርጫ 97 ጋር በተያያዘም በመላው ሃገሪቱ የተካሄደው ግፍና ጭፍጨፋ ዛሬም ድረስ እንቅልፍ ይነሳናል። በየገጠሩና በየመሃል ሃገሩ በተናጠል እየታደኑ የሚታሰሩት የሚገደሉትና የሚሰወሩት ወገኖቻችን ህይወት ያሳዝነናል።

የሃገሪቱ ብርቅዬ ልጆች እየተመነጠሩ ለእስር ሲዳረጉና ሰቆቃ ሲፈጸምባቸው ስናይ እልክ ይተናነቀናል።

ዛሬም የፍትህ ያለ በሚል አንጀታቸው ጭምር እያለቀሰ የሚገኙትና የሙታን ሰማእታቱ እርዳታ የጎደለባቸው እናቶች አባቶች  እንዲሁም መላ ቤተሰቦች የልጆቻቸው ደም ደመ ከልብ ሆኖ የመቅረቱን ያህል እንደሚሰማቸው ይታወቀናል።::

የደም አበላ በወረደባት ሃገራችን ኢትዮጵያ የግድያው አዛዦችና መሪ ከያኒዎች የዛን ሁሉ ዜጋ ደም አፍሰው የብርጭኮ ውሃ እንኳ እንዳልተደፋባቸው በመቁጠር ያን የገዘፈ የህዝብ ፍጅት ተኩራርተውበታል። ቀልደውበታል። ልክ አገባነው ብለው ፎክረውበታል።

ክቡር የሆነው የሰው ልጅ ግንባር ግንባሩን በጥይት እንዲመታ ትእዛዝ ሰጥተው ዴሞክራሲያችን ልጅ ስለነበረ ነው፣ ውሃ የሚረጭ መኪናና የሰለጠነ የሰው ሃይልም ስላልነበረን ነው በማለት አፌዘውበታል።

ዛሬ በመላው ሃገሪቱ በረሃብ አለንጋ እየተጠበሰ ያለው ወገን የትየለሌ ሆኖ ሳለ ራሳቸውን ልማታዊ መንግስት ብለው የሰየሙት እነሂ ገዳይና ዘራፊ ገገርዎች መልካቸውን እየለዋወጡ ዝንተ አለም ስልጣን ላይ ተቀምጠው

ፍትህ የጠማውን ተጠቂ ማፈናቸው ነገም ለዴሞክራሲያዊ ሙብቱ ብቅ ሲል አንቅ ሊያራጉት እየተዘጋጁ ለመሆናቸው ሃገር የሚያወቀው ጉዳይ ነው።

ሴቲቱን ልንወልድባት መሬቷንም ልናርስበት ብለው ዘረኛ ተልእኳቸውን ከሰሜኒዊው ኢትዮጵያ ምድር የጀመሩት እነኚህ ነውረኛና ዘረኛ ገገርዎች ዛሬም በመላ ሃገሪቱ ነፍጥን ተገን አርገው ተመሳሳይ ተግባራትን እየፈጸሙ መሆናቸውን ፤ካለሞያቸውም በተማረው ወገን አናት ላይ ተቀምጠው ፈላጭ ቆራጭ መሆናቸው ወገን የተገነዘበው ሃቅ ነው።

ከውልደታቸው አንስቶ እስከዛሬ ድረስ የገዳዮቹን ዘረኛ ስርዓት ለመረመረ እጃቸው በደም የተነከረ በሃገር አንድነትና በህዝብቿ ታሪክ ላይ ያለቸው አመለካከት የተጭበረበረ በስልጣን ላይ ለመቆየት ይመቻቸው ዘንድም በሃገሪቱ ዳር ድንበር ላይ የተደራደሩ በስልጣን ላይ እስካሉም ድረስ እየገደሉና እየመዘበሩ ሊኖሩ የመረጡ ጎሰኞች መሆናቸውን እንረዳለን።

የተከበራችሁ ውድ ኢትዮጵያውያን

የ200 ዜጎችን ህይወት በአንዲት ጀንበር በቀረጠፈ በአምስተኛ አመቱ ሙሉ የፓርላማ ወንበሮችን አሽንፍኩ ያለው የዘረኛ ወንበዴዎች አገዛዝ ዴሞክራሲያዊ ሙብትን ያገናጽፈናል ብሎ ህዝባችን እንደማያምን እንረዳለን።

በመላው አለም ያየናቸው አምባገነኖች በህዝባዊ አመጽ ሲወጠሩ በቀላሉ ጥለው መፈርጥጣቸውን ብናውቅም ይሄ በህዝባችን አናት ላይ የተንሰራፈው አምባገነን ስራት ግን ዘረኛ በመሆኑና ከራሱ ዘር በላይ ስለሌላው ዘር ደንታ የለውምና የጅምላ ፍጅቱን መቸውም ቢሆን ለመፈጸም በተጠንቀቅ ላይ እንደሆነ ወገን ሁሉ ይረዳል ብለን እናምናለን።

ወይ እንደወንዶቹ ጠመንጃ ይዘው ይፋለሙናል አለበለዚያም ጨርቃቸውን ጠቅልለው ካሃገር ይለቁልናል የሚለው የአምባገነኑ ገዢ ሃይለ ቃል የሚያመለክተዉም ይህንኑ ነው።

ቀድሞ ስለአምባገነኖች የተናገርነውን እንድገመውና

አምባገነኖች እስካሉ ድረስ

በተቃዋሚ ሃይል ላይ ስም ይለጠፋል። ከፀረ ሰላም፡ ከሽብር ፈጣሪነት፡ ከትምክህተኛነት ይመደባል

ሰላም አንደማይኖር ይረጋግጣል፣ በሃገር ላይ ያለ መረጋጋርት ይሰፍናል

የህግ የበላይነት ይገሰሳል፣ ተቻችሎ የመኖር ባህል ይጠፋል፣ ዜጋ ያለ ህግ ይጋዛል፣ ይሰደዳል

በምድሪቱ ላይ በግፍ የሚፈሰው የዜጎች ደም ይበረከታል፣ ሃገር ሁሌም በጦርነት አንደታመሰ ይኖራል

በሚፈጥሩት ኢፍትሃዊነት ሳቢያም ህዝቦች አርስ በርስ አንዲጫረሱ መንገድ ይመቻቻል፣

የሰላምና የእርቅ ዘንባባ ሳይሆን ሰይፍና ጥይት ይበረከታል፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ይህ በህዝባችን ላይ የወረደ የአምባገነኖች መአት ተወግዶ ዜጋ የሰላም አየር ይተነፍስ ዘንድ ቀድሞም የጀመረውን ትግል በአዲስና በተጠናከረ መልክ አሻሽሎት ይገኛል።

የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር የዚህን ገዳይ አምባገነን ስራት መሪዎች ለመቅጣትና ስራታቸውንም ጥሎ አዲስና ዴሞክራሲያዊ መንግስት በሃገራችን ላይ እስኪቆም ድረስ የወጠነውን ልዩ የትግል ጉዞ "ዘመቻ ደመላሽ " ብሎ ሰይሞታል።

1. ዘመቻ ደመላሽ የኢትዮጵያን ህዝብ ከገዳዮችና ካሽባሪዎች ይከላከላል
2. ዘመቻ ደመላሽ እጃቸው በንጹሃን ደም ከታጠቡ የህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ ዘረኛ ገዢዎችና ከነሱም ጋር የወገነዉን ወንጀለኛ ከህዝብ ጋር በመተባበር እያሳደደ ይቀጣል
3. ዘመቻ ደመላሽ ጠዋሪና ደጋፊ ልጆቻቸው በህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ ገዳዮች የተሰዉባችዉን ቤተሰቦች ያብሳል፣ያጽናናል፣ያስተባብራል፣ይረዳል በደረሰበትም የሰማእታቱን ሃውልት ያቆማል።
4. ዘመቻ ደመላሽ ህዝቡ ራሱን ከገዳዮች ይከላከል ዘንድ ያደራጃል ያስታጥቃል።፣
5. ዘመቻ ደመላሽ ነጻ በሚያወጣቸው አካባቢዎች ህዝቡ በተረጋጋ መንፈስ የለት ተለት ህይወቱን ይመራ ዘንድ ከሌሎች የሃገሪቱ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ዴሞክራሲያዊ ማእከላት እንዲቋቋሙ ይረዳል
6. ዘመቻ ደመላሽ የዛሬዎቹን ደም አፍሳሾችና ዘራፊዎች የገቡበት ገብቶ ለፍርድ የሚያቀርብ ግብረ ሃይል ያደራጃል ያስተባብራል።

የተከበራችሁ የህዝባችሁ መንገላታትና የነጻነት እጦት የሚያንገበግባችሁ ኢትዮጵያውያን በሙሉ

የድርጅቱንና የአመራር ጥራቱን በመጠበቅ የሚንቀሳቀሰው ዘመቻ ደመላሽ ተልዕኮው የተሳካ እንዲሆን የናንተን የወገኖቹን የገንዘብ አስተዋጾ ይሻል።

በመሆኑም ድርጅቱ መክሮበትና በጥንቃቄ ተወያይቶበት ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለበት ደረጃ በጀመረው በዚህ የወገን ደራሽ ዘመቻ በሚከተሉት ሃገሮች የሚገኙትን ተወካዮች ስልክ ቁጥር በመደወል ልባዊና ያልተገደበ ኢትዮጵያዊ የገንዘብ ድጋፋችሁን ታደርጉ ዘንድ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር የዘመቻ ደመላሽ አስተባባሪ ግብረ ሃይል ጥሪውን ያስተላልፋል።

1/ እስራኤል 972543928604

2/ ኖርዋይ 4741467212 ወይንም 4745556909

3/ ስዊድን 46707403606

4/ ኔዘርላንድ 31685158659

5/ ቤልጂየም 32493499619

6/ ጀርመን 4915253814296

7/ ለንደን 447875577686

7/ አሜሪካ ኒው ዮርክ 13472061823

8/ አሜሪካ ተነሲ 16154237079

9/ አሜሪካ ሳንዲየጎ 16193686655

10/ አሜሪካ ፊላደልፊያ 12157659590

11/ ካናዳ 19059234721

12/ አውስትራሊያ 61421872776

በዚህ አጋጣሚም ህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ ሊወገድ የሚችለው በታጠቀ ሃይል ብቻ መሆኑን የሚያምን ማናቸውም ልቡ የነደደ ዜጋ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባርን ሳይውል ሳያድር በመቀላቀል የህዝባችንን የጣዕር እድሜ ያሳጥር ዘንድ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ለተጨማሪ መረጃ www.arbegnochginbar.com ይጎብኙ።

## የኢትዮጵያ ህዝብ ተነስ

## አንድነት ሃይል ነው

## ዘመቻ ደመላሽ በአጭር ጊዜ ግቡን ይመታል

## የዘመቻ ደመላሽ አስተባባሪ ግብረ ሃይል